# የቅንጅት አፈንጋጮች የአንጃ ፓርቲ ለማቋቋም እየተራወጡ ነው፡፡

ለወያኔ የጎሳ መርህ አገዛዝ የጠላት መሳሪያ ለመሆን ወስነው ከቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ያፈነገጡ ጥቂት አመራር አባላት ባሁኑ ወቅት በቡድን ተሰባስበው ሕገ ወጥ ፓርቲ ለማቋቋም በመራወጥ ላይ እንደሚገኙ ሰሞኑን ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሱን መረጃዎች አመልክተዋል፡፡

እንደ ውስጥ አዋቂ ምንጮች አገላለፅ የአንጃው አባላት አዲስ ፓርቲ ለመመስረት እንዲያስችላቸው ፊርማ ለማሰባሰብ የመንቀሳቀሻ ደብዳቤ እንዲጻፍላቸው እንዲሁም የፊርማ ቅፅ እንዲሰጣቸው ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማመልከታቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ በይርጋዓለም ከተማ ተገኝተው በጠሩት ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ 15 ሰዎች ብቻ የተገኙላቸው ሲሆን እንዲሁም በአዋሳ ተመሳሳይ ጥሪ አድርገው ከ22 በላይ ሰው እንዳላገኙ የቅንጅት አባላት ከሥፍራው ገልፀዋል፡፡

በተዛመደ መልኩ የአንጃው አባላት ለአፍራሽ ዓላማቸው መሣሪያ የሚሆኑ መሰሎቻቸውን ለማፈላለግ ለመስክ ስምሪት በየክልሉ ሰዎች መመደባቸውን ውስጥ አዋቂ ምንጮቻችን በተጨማሪ ተናግረዋል፡፡

በዚህም መሠረት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያምንና ወ/ሪት ብርቱካንን ጨምሮ 15 ግለሰቦች የሚገኙበት ቡድን ወደ አማራ ክልል የሚሄድ ሲሆን ዶክተር ኃይሉ አርአያን ያካተተው 7 ግለሰቦች ያሉበት ቡድን ደግሞ ወደ ደቡብ ኦሮሚያ እንደሚያቀና ታውቋል፡፡

እንዲሁም 4 ግለሰቦች የሚገኙበት ቡድን ወደ ምሥራቅ ኦሮሚያ የሚላክ ሲሆን 2 ግለሰቦች ወደ አፋር የሚሄዱ መሆኑን ከምንጮቻችን ተጠቅሷል፡፡

በተያያዘ መረጃ አቶ ሙሉነህ ኢዩኤልና አቶ ተመስገን ዘውዴ የሚገኙበት ቡድን ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ እንዲሄድ የተመደበ ሲሆን በአዲስ አበባ እንዲንቀሳቀሱ የተመደቡ ግለሰቦችም መኖራቸው ታውቋል፡፡

አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች በአሁኑ ወቅት የአንጀኞቹን እንቅስቃሴ በማስመልከት ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት አስተያየት ድካማቸው ሁሉ ገዥውን ፓርቲ ለማስደሰት መሆኑን አስረድተው ሕዝባዊ መሠረት ስለሌላቸው ጋት እንኳን ሊጓዙ እንደማይችሉ በእርግጠኝነት ተናግረዋል፡፡

ዘግይቶ በደረሰን መረጃ መሰረት ለምርጫ ቦርድ አቅርበውት የነበረው ማመልከቻ በፓርቲ ስያሜ እና በውስጠ ደንብ አለመኖር ምክንያት ውድቅ የሆነባቸውና በአሁኑ ወቅት የፓርቲ ስም አውጥተውና ደንብ አጽድቀው ያቀረቡ መሆናቸው ተገልጿል፡፡

አፈንጋጮች ቀደም ሲል መኢአድ ከቅንጅት ተገንጥሎ ለመውጣት ተግባራዊ እንቅስቃሴ የጀመረ አስመስለው ሲያወሩ ቆይተው አሁን ግን እነርሱ በአንጀኝነት እራሳቸውን ከቅንጅት ፓርቲ መገንጠላቸው በዙዎችን አስገርሟል፡፡

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com